ይድረስ፡- ለአቶ ብንያም ምሕረት!

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ "ዮም ፍሥሓ ኮነ! በእንተ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኵላ ምድር፡ ዘኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር!" እያለች፡ ሰላምታዋንና የእግዚአብሔር እውነት የኾነችውን፡ ኢትዮጵያዊት መልእክቷን፡ በእናትነት ፍቅር፡ እንዲህ በማስቀደም ታቀርብልዎታለች።

በፌስቡክ መድረካችን ላይ፡ ስለጻፉልን ትችት፡ "እግዜር ይስጥልን!"

እነዚህን የመሰሉት የነቀፌታ ትችቶችና መጠይቃውያን አስተያየቶች፡ አያሌ፡ የተደበቁ፡ የእግዚአብሔር እውነቶች እንዲከሠቱ ስለሚያደርጉ፥ ስለሚያስችሉም፡ በጣሙን ይጠቅሙናል፤ ያስፈልጉናልም። ምክንያቱም፡ አንዳንድ ጊዜ፡ የነቀፌታው ትችትና የመጠይቃዊው አስተያየት አቅራቢዎች፡ በምንሰጣቸው ምላሾች ረክተው፡ ወደእግዚአብሔር እውነት የማይመለሱ፡ አንገተ ደንዳናዎች፡ አልፎ አልፎ ቢገኙም እንኳ፡ ከአንባቢዎች መካከል፡ አውቀውና ተረድተው፥ በንስሓም፡ ወደዚችው፡ ወደእግዚአብሔር እውነት ሊመለሱ የሚበቁ፡ ብዙ አስተዋዮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው፡ የነቀፌታ ትችቶቹና መጠይቃውያኑ አስተያየቶች፡ "ይጠቅሙናል፤ ያስፈልጉናልም!" ያልነው።

አዩ፡ አቶ ብንያም!

፩ደኛ፡ አቶ "አያሌው ወርቁ" የተባሉ መሰልዎና ተባባሪዎ፡ በግብረ ዐበርነትና በተከታይነት፡ *"አቡነዘ በሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጣ መንግስትከ ወይኩን ፈቃድከ ከማሁ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳዬነ ዘእለለ እለትነ ሀበሳየነ ወጀጋዬነ ከመድህነኒ እግዚኦ ውስተ መንሱት ኣላድነነ ወባላሀነ እንኩልኩይ ስመ እግዚአ'ከ ይቲ መንግስት ሀሎስብሀት ለአለም አለም አሜን። 3ጊዜ"* ሲሉ የጻፉትን በማከል፣

፪ተኛም፡ እርስዎ፡ *"ትክክለኛዉን ዉሰድ....አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምፃእ መንግስትከ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለእለትነ ሀበነ ዮም። ህድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንህነኒ ንህድግ ለዘአበሰ ለነ። ኢታብአነ እግዚኦ ዉስተ መንሱት። አላ አድህነነ ወባልሀነ እምኩሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግስት ሃይል ወስብሀት ለአለም አለም!!!*

*"በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በህሊናኪ ወድንግል በስጋኪ ። እመ እግዚአብሄር ፀባኦት ሰላም ለኪ። ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ ። ተፈስሂ ኦ ምልእተ ፀጋ እግዚአብሄር ምስሌኪ ። ሰአሊ ወፀልዩ ሃበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይስረይ ለነ ሃጣዉኢነ ።*

*"ትክክለኛዉ ይህ ነዉ ይህን ዉሰድ!!! የክህደትህን መርዝ እዚህ አትዝራ!!!"* በማለት፥ በድፍረትና በማናለብኝነት፡ የሠነዘሩትን፡ የነቀፌታ ትችትዎን መልእክት፡ ከላይ በገለጽነው መልክና ይዘት፡ በኹለንተናው ተቀብለን፡ በአግባቡ የምናስተናግደው ሲኾን፡ አቀራረቡ ግን፡ ከእግዚአብሔራዊው ኢትዮጵያዊ ሥርዓታችን ውጭ በመኾኑ፡ ይህንኑ አቀራረቡንና መንፈሱን፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ያልተቀበልነው መኾኑን፡ አስቀድመን ልናሳውቅዎ እንወድዳለን።

በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ እርስዎ፡ ይህን የመሰለውን፡ የነቀፌታ ትችት ከመሠንዘርዎ በፊት፡ ቀደም ብለው፡ ሊያደርጉት ይገባዎት የነበረው ግዳጅ፡ ስለዚሁ ርእስ የተጻፉትን፡ ሰፋፊ ሓተታዎችንና ማብራሪያዎችን የያዙትን ዕትሞቻችንንና የጎዋ መልእክቶቻችንን ማንበብን ነበረ።

ነገር ግን፡ ይህን ፈጽመው ስላልተገኙ፡ ሌላው ግዳጅዎ ሊኾን ይገባ የነበረው፡ *"ኧረ! ይህ፡ የቀድሞው፡ የ'አቡነ ዘበሰማያት' ጸሎት፡ እንዲህ ኾኖ፡ ተለውጦ የቀረበበት ምክንያት፡ ከቶ ምንድር ነው?"* የሚል ጥያቄን ማቅረብን ብቻ ነበር።

በዚያ መልክ ቀርቦ ቢኾን ኖሮ፡ በዚያን ጊዜ፡ በእኛ በኩል፡ ተገቢውን መልስ፡ በቀጥታ ለመስጠት፡ ባመቸን ነበር። ዳሩ ግን፡ ባለመታደል፡ እንዲያ ሳይኾን በመቅረቱ፡ መልሳችን፡ ከዚህ በሚከተለው ኹኔታ እንዲቀርብልዎ፡ ግድ ኾኗልና፡ ይህንኑ፡ በጨዋነትና በማስተዋል ይመልከቱት!

በዚህ ረገድ፡ በቅድሚያ ልናቀርብልዎ የምንፈልገው፡ ቀለል ያለ ጥያቄ አለ። ይኹን እንጂ፡ ከራስዎ፡ የጥያቄ አቀራረብ የተነሣ፡ ለዚያ፡ ቀላል ጥያቄያችን እንኳ፡ ቀላል የኾነውን መልስ ለመስጠት፡ የሚችሉ አልመሰለንም። እንዴት ይችላሉ? አይችሉም። ይህንም እውነታ፡ ከዚህ በመቀጠል ያሠፈርነው አስተያየት፡ ያስገነዝብዎታል፡-

ለዚሁ አስተያየታችን፡ ቀዳሚ የምናደርገው መግቢያ፡ *"ትክክለኛዉ ይህ ነዉ ይህን ዉሰድ!!! የክህደትህን መርዝ እዚህ አትዝራ!!!"* የሚለውን፡ ዘለፋን የተላበሰውን፡ የራስዎን፡ የነቀፌታ ትችት ይኾናል። እዚህ ላይ፡ እርሱን፡ በምሳሌነት ወስደን፡ "ይህ የትችት አባባልዎ፡ 'የመንፈስ ቅዱስ ነውን?' ወይስ፡ የሌላው መንፈስ? 'የማን ነው?' ብለው ይገምታሉ? የማንስ ይመስልዎታል? እስኪ፡ ራስዎን እንጠይቅዎት!" ብለን የምናቀርብልዎ፡ አግባብነት ያለው ጥያቄያችን፡ ተከታዩ ይኾናል።

ታዲያ! ለዚህ ጥያቄያችን፡ የሚሰጡን መልስ፡ ምን ዓይነት እንደሚኾን፡ የራስዎ፡ የጥያቄ አቀራረብና አገላለጽ ሳይቀር፡ ራስዎን፡ ስላስገመተዎት፡ "አስቀድመን፡ ልናውቀው እንችላለን!" ብንል፡ የተሳሳትን አይመስለንም።

አዎን! እንኳንስ፡ ይህን፡ ሰፊና ጥልቅ የኾነውን፡ ሃይማኖታዊ ምሥጢር ለያዘው ጥያቄያችን፡ በቂ መልስን ሊሰጡ ቀርቶ፡ ያመኑበትንና "እራሴ እጸልየዋለሁ!" ያሉትን ጸሎት እንኳ፡ በትክክለኛው የሥነ ጽሕፈት መልኩና ይዘቱ፡ አከናውነውና አሟልተው ማቅረብ እንዳልቻሉ እኮ አየን። ያም ብቻ አይደለም፤ በነጥቦቹና በሥነ ሆህያቱ፥ እንዲሁም፡ በሥነ ፊደላቱና በቃላቱ አጻጻፍ ረገድ እንኳ፡ የግእዙም ኾነ፥ ኢትዮጵያኛው ሥርዓታት እንዳልተጠበቁም ተመለከትን።

እንዲያው ለመኾኑ፡ ይህንኑ፡ የ"አቡነ ዘበሰማያት"ን እና የ"ኦ እግዝእትየ ማርያም"ን ጸሎታት፡ በቃልዎ፥ ወይም፡ በንባብ፡ በሚደግሟቸው ጊዜስ፡ ምን እያሉና እንዴት እያደረጉ ነው የሚጸልዩዋቸው? ለመኾኑ፡ ምንባቡ፡ እንዲህ ተቃውሶና ማስኖ፡ በግእዙ ሲጸልዩዋቸው፡ ትርጉሙ እየገባዎት ነውን? ወይስ ሳይገባዎት የሚጸልዩዋቸው?

በእኛስ በኩል ደግሞ፡ ይህንኑ፡ ዘለፋን የተላበሰውን፡ የነቀፌታ ትችትዎን፡ "የመንፈስ ቅዱስ ነው? ወይስ፡ የሌላው መንፈስ? 'የማን ነው?' እንበል!" ለሚለው ጥያቄያችን፡ የእርስዎን መልስ ሳንጠብቅ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንዲህ እያለች፡ ትገልጥልዎታለች፡-

አብወእም የኾነው፡ አንዱ፡ ቸሩ አምላክ እግዚአብሔር፡ እርስዎን፡ ገና በማሕፀን፡ <u>በእርሱ መልክ፡ በነፍስና በሥጋ፡ ከፈጠረዎ በኋላ፥</u> "ከእኛ እንደአንዱ ኹነ!" ብሎ፡ <u>ነፍስዎንና ሥጋዎን፡ በተዋሕዶ፡ አንድ በሚያደርጋቸው፡ በቅዱስ መንፈሱ የወለደዎ ነዎት</u>። በተፈጥሮዎ፡ እንዲህ ፍጹም ሲኾኑ፡ እርስዎ ግን፡ እግዚአብሔርን ለሚያስመስልዎ፡ ለመልካሙ ብቻ ሊያውሉት ይገባዎ የነበረውን፥ በሥነ ተፈጥሮ፡ ያገኙትንም፡ ያን፡ የእውነት መንፈስ፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪዎ፡ በፍቅር ልግሥና፡ በተሰጠዎት የአምላክ ልጅነትዎና የመምረጥ ነጻነትዎ ሥልጣን ተጠቅመው፡ በመልካምነቱ እንዲቀጥል የሚያስችለውን በጎ ምርጫ ማድረግ ሲገባዎ፡ ያን፡ "አልፈልግም!" ብለው፡ "ርኵስ" ወዳሰኘው ክፋትነት ለወጡት፤ "ሰይጣን" አሰኙተውም፡ በፈቃድዎ፡ ለዲያብሎስ አስገዙት።

ገና በማሕፀን ሣሉ፡ እንዲህ፡ በንጽሕናና በቅድስና፡ ከፈጣሪዎ የተሰጠዎትን፥ እርስዎም፡ በዚያው መልክና ይዘት፡ የተቀበሉትን፡ ያን፡ የተቀደሰ መንፈስዎን ነው፡ እንግዴህ፡ ኋላ፡ "ርኵስ" ወዳሰኘው ክፋትነት ለውጠው፥ "ሰይጣን"ም አሰኙተው፡ ያን የመሰለ፡ የነቀፌታ ትችትን፡ እንዲያ፡ በድፍረትና በማናለብኙነት፡ እንዲሠነዝሩ ያደረገዎት። ይህም የኾነው፡ የሊቀ ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ የተቀደሰ መንፈስ፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተቃወመ ጊዜ፡ በጌታችን ኢየሱስ መሢሕ አንደበት፡ **"ሑር እምድኅሬየ፡ ሰይጣን! እስመ ኮንከ ማዕቅፍየ፤ እስመ ኢትሔሊ ዘእግዚአብሔር፥ ዘእንበለ ዘሰብእ።"** ማለትም፡ **"አንተ ሰይጣን! ከኋላዬ ወግድ! የሰውን እንጂ፡ የእግዚአብሔርን አላሰብህምና።"** ተብሎ፡ እንደተገሠፀው፡ ማለት ነው። (ማቴ. ፲፮፥ ፳፩-፳፫።)

ይህ ሰይጣናዊ መንፈስ ነው፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ አማካይነት፡ ከዛሬ፡ ሦስት ሽህ ዓመታት ጀምሮ፥ በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች አማካይነት ደግሞ፡ ከዛሬ ሽህ ስድስት መቶ ዓመታት አንሥቶ፡ በቀደመው ቍስል ላይ፡ ሌላ ጽኑ ቍስልን በመጨመር፡ ኢትዮጵያውያንን እና ኢትዮጵያውያትን፡ ለክፎና ተፃርሮ፡ ለዚህን ያህል ዘመን፡ እንዲህ እያናከሰና እያባላ፡ በነፍስና ሥጋ፥ በመንፈስም፡ ሲጠናወታቸውና ሲያሽመደምዳቸው፥ ሲያጥመነምናቸውና ሲያማቅቃቸው የኖረው።

ይኸው፡ ጕሥቍልና፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ እንዲህ የቀጠለው፡ እየራሳቸውን፡ በሓሰት፡ "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!" የሚሉትን፡ እርስዎንና እርስዎን የመሰሉትን ኹሉ፡ አካትታ በያዘችው፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፡ ቅርንጫፍ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መኾኑ፡ በእውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ በይፋ የሚታወቅ ነው።

ይህን እውነታ፡ እስካኹን፡ እርስዎ አላወቁት እንደኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ማወቅ ብቻ አይደለም፡ በጥብቅ ሊገነዘቡትም ይገባል።

ታዲያ! በሐሰት፡ "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!" በሚሉት፡ እርስዎንና እርስዎን የመሰሉትን ኹሉ አካትተው በያዙት፡ በእነዚያ፡ የሦስት ሽህ ዓመታት ትውልዶች ዘንድ፥ የዛሬውንም ትውልድ ጨምሮ፡ እንዲህ፡ በስድብና በነቀፌታ፥ በጥላቻና በቂም በቀል ብቻ ካልኾነ በቀር፥ አዎን! በመጨረሻውም፡ እርስ በርስ፡ ደም በመፋሰስና በመተላለቅ ካልኾነ በቀር፡ በአይሁድ ኦሪታዊነቱ፡ ለሽህ ዓመታት፥ በግብፃውያን ኦርቶዶክስ ክርስቲያንነቱ ደግሞ፡ ለኹለት ሽህ ዓመታት፥ በድምሩ፡ ለሦስት ሽህ ዓመታት፥ እስከዛሬና ዛሬም ድረስ፡ በእኒሁ፡ "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!" በሚሉት፡ እርስዎንና እርስዎን በመሰሉት ሓሳውያን መካከል፥ አኹንም እንኳ፡ በእርስዎና በእኛ መካከል እየኾነ እንዳለው፡ እንዴት፡ በሰላምና በፍቅር፡ ለመቀራረብና ለመገናኘት፥ ቍጭ ብሎና "እህ!" ተባብሎም፡ በመደማመጥ ለመነጋገርና ለመወያየት ሳይቻል ቀረ?

"**ዘቦ ዕዝን፡ ሰሚዓ ለይስማዕ!**" ማለትም፡ "**የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!**" ያለውን፡ የመምህራችንን፡ የመሢሕ ኢየሱስን ቃል፡ እርስዎም ኾኑ፡ እርስዎን የመሰሉት ኹሉ፡ ሰምታችሁ የምትፈጽሙት ከኾነ፡ ይኸ እውነታ፡ ምን ዓይነቱን፡ ለሦስት ሽህ ዓመታት ተደብቆ የኖረ የጉድ ምሥጢርን እንዳወጣ፡ እስኪ እንንገርዎ! (ማቴ. ፲፩፥ ፲፭።)

**ይኼም ምሥጢር፡** እንደእርስዎና እርስዎን እንደመሰሉት፡ እንደዛሬዎቹ አስመሳዮችና ግብዞች፡ "ሀገረ እግዚአብሔር፥ ሕዝበ እግዚአብሔር፥ መንግሥተ እግዚአብሔር" በተባለችው፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ ያለማቋረጥ በተካኼዱት፡ እነዚያን፡ ከላይ የተጠቀሱትን በመሰሉት፡ አሠቃቂና ዘግናኝ፥ አስነዋሪና አሳፋሪ በኾኑት፡ የግድያና የዕልቂት ድርጊቶች የተሞላው ዜና መዋዕል፡ የሰዎች ደም ፈስሶ፡ ያን ጠጥቶ መርካትን የሚወድደው፡ <u>የርኩሱ መንፈስ፡ የክፋትና የጭካኔ፥ የጥፋትና የሞት ሥራ የተፈጸመበትና የተከሠተበት እንጂ፡ የመንፈስ ቅዱስ አለመኾኑን፡</u> የሚያረጋግጠው ነው።

አዎን! ይህን እውነታ፡ እርስዎ ራስዎ ጭምር፡ ሃይማኖታዊ ማስረጃ አድርገው፡ በምስክርነት ሊቀበሉት የሚችሉት እንደሚኾን እናምናለን።

የዛሬ ኹለት ሽህ ዓመት ገደማ፡ መጥምቁ ዮሓንስ፡ "**አ ትውልደ አራዊተ ምድር! መኑ አመረክሙ፡ ከመ ታምሥጡ እመቅሠፍት፥ ወእመንሱት፥ ወእመዐት ዘይመጽእ። ግበሩኬ እንከ፡ ፍሬ ሠናየ፡ ዘይደልወክሙ፡ ለንስሓ።**"

ማለትም፡ "**እናንት የምድር ዐውሬዎች ልጆች! ከሚመጣው መቅሠፍት፥ ጥፋትና ቍጣ የምትድኑበትን መንገድ፡ ማን አመለከታችሁ? እንግዴህ፡ ለንስሓ የሚያበቃችሁን መልካሙን ፍሬ አድርጉ!**" ብሎ የተናገረውን፥ የማስጠንቀቂያ ቃል፡ በዘመኑ የነበረው፡ ክፉና ከሃዲ፣ ዓመፀኛና የአምልኮ አመንዝሬ ትውልድ፡ ሰምቶ እንዳልተቀበለ ይታወቃል። (ማቴ. ፫፥ ፯-፰።)

ታዲያ! እንደዚያኑ ጊዜ ኹሉ፡ እርሱን መስሎ የተገኘውና "አ ትውልደ አራዊተ ምድር!" ማለትም፡ "እናንት የምድር ዐውሬዎች ልጆች ሆይ!" የተባላችሁትን፡ እንደእርስዎ ያሉትን ዐንገተ ደንዳኖች ያጠቃለለው፡ ይኼ፡ የዛሬው፡ ክፉና ከሃዲ፥ ዓመፀኛና የአምልኮ አመንዝሪ ትውልድ፡ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የምታስተላልፍለትን፡ የምሕረትና የምሥራች መለኮታዊ ቃል ሰምቶ፥ እናንተም፡ በእየራሳችሁ ሰምታችሁ መቀበልን፡ "እምቢ!" ብላችሁ፡ ሳትፈጽሙት የምትቆዩት እስከመቼ ነው? የ፪ሺ፯ (የኹለት ሽህ ሰባት) ዓመታት ረዥም ዕድሜ እንኳ፡ ለዚህ ታላቅ የንስሓ ዕድል፡ እንዴት፡ አኹንም ገና የሚያበቃችሁ ሊኾን ሳይችል ቀረ? አለመቻሉ፡ አዎን! ማስደነቅ ብቻ አይደለም፤ እጅግ ያስገርማልም፤ ያሳዝናልም እንጂ።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከኪዳነ አዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ እስከዛሬ ያካኼደችው የተልእኮዋ ውጤት፡ እንዲህ፡ እርስዎንና እርስዎን የመሰሉትን "ክርዳድ" የተባሉትን፡ እንክርዳዶች ማብቀሏ አይደለም። የእርሷ፡ የኢትዮጵያና የእግዚአብሔር "ዘርእ-ሠናይ፥ ሥርናይ" የተባሉትንና በመልካም ዘርና ስንዴ የተመሰሉትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ልጆችን ማፍራቷ እንጂ።

እኒህም፡ የ፯ሺ፭፻፯ (የሰባት ሽህ አምስት መቶ ሰባት) ዓመታት ዕድሜ ባለጸጋ በኾነችው፥ ደግሞም፡ ምንጊዜም፡ በመላው የዓለም ምድር ላይ፡ ተዘርግታና ሰፍና በምትገኘው፡ በራሷ፡ በቅድስት ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ፡ ተዘልለውና ተዝናንተው፡ በፍጹም ነጻነትና ሰላም፥ ፍቅርና ደስታ፥ ዕረፍትና ምስጋና፡ እየኖሩ ያሉት፥ በአያሌ እልፍ አእላፋት ብዛትም የሚቆጠሩት፥ ህልውናቸውንም፡ በቅድስቲቱ የትንሣኤ ሕይወት እና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም እንዲቀጥሉ ያደረገችላቸው ልጆቿ ናቸው። (ማቴ. ፲፫፥ ፳፬-፴፫።)

የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ ይህችው ኢትዮጵያ፡ መለኮታዊውና መሠረታዊው፥ አጠቃላዩና ዘለዓለማዊዉም ተልእኮዋ፡ ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ መጻሕፍቷን፥ እንዲሁም፡ በጎዋ ሰሌዳዋና መድረኮቿ፥ የጥያቄና መልስን በመሰሉት፡ ልዩ ልዩ ዓምዶቿም አማካይነት የምታስተላልፋቸውን መልእክቶቿን ኹሉ፡ በተቻለ መጠን ማንበብን ይጠይቃል።

እርስዎና እርስዎን የመሰሉት እንክርዳዶች ኹሉ ግን፡ እንዲህ፡ እንደእነዚህ፡ ከላይ እንደተጠቀሱት፡ እንደእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እየተከታተላችሁ በመፈለግ፥ አግኝታችሁ በማንበብ፥ አውቃችሁም በመጠየቅ፡ ተረድታችሁ ቢኾን ኖሮ እኮ፡ ይህን የዛሬውን የተሳሳተ ጥያቄዎን ለማቅረብ፥ ባልደፈሩም፥ እንዲያውም፡ ባላስፈለገዎትም ነበር።

ስለዚህ፡ በእርስዎ በኩል፡ ይህን ፊተኛ የማወቅ ግዳጅ፡ በቅድሚያ ከፈጸሙ በኋላ፡ ከመጨረሻው፡ ፍሬያማ ግብ ለመድረስ፡ ከዚያ አያይዘው፡ ራስዎን፡ ከዚህ፡ ከ፫ሺው (ከሦስት ሽሁ) ዓመታት፡ የኦሪታዊው ይሁዲነት፥ ደግሞም፡ የእርሱ ማጠናከሪያ ግብረ ዐበሩ ከኾነው፡ ከ፩ሺ፮፻ው (ከአንድ ሽህ ስድስት መቶው) ዓመታት፡ የኦርቶዶክሳዊው ግብፃዊነት ጽኑ ቀንበር፡ ፈጽመው ነጻ አድርገው፡ የ፯ሺ፭፻፯ቱ (የሰባት ሽህ አምስት መቶ ሰባቱ) ዓመታት ዕድሜ፡ ባለቤት የኾነውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን መቀዳጀት ይኖርብዎታል።

ከዚህ በኋላ፡ በዚህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትዎ፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ የመንፈስ ቅዱስ የኾነውን እውቀት፡ በርቅቀትና በግህደት፡ ስትገልጽልዎ ይገኟታል። በዚያን ጊዜ፡ ኹሉን፡ በፍጹምነት ስለሚያውቁ፡ የሚጠይቁት፡ አንዳች ነገር፡ ከቶ አይኖርም።

በዚህ ረገድ ያለውን አላዋቂነትዎን አያስተውሉትምን? እርስዎ የሚሉትን፡ "የአቡነ ዘበሰማያት"ን ጸሎት፡ ሓዋርያቱ ስለጠየቁት፡ እርሱው፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ አዘጋጅቶ አስተማራቸው፤ ደግሞም፡ እነርሱ ሳይኾኑ፡ እርሱው ጸልዮ፡ የመጨረሻና የተሟላ፥ ፍሬያማና መልካም የኾነውን የመልስ ውጤቱን፡ በራሱ ቤዛነት አስገኘ። ከዚህ የተነሣ፡ ይህ ጸሎት፡ እንግዲህ፡ ለአንደኛውና ለመቼውም ጊዜ፡ ተፈጽሞና ተጨርሶ ያበቃለት ኾኗል። ያበቃለትም፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ሰባት ዓመት መኾኑ፡ እንዲህ፡ ተረጋግጦ እየታወቀ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ኹሉ፡ አኹንም ገና እየጸለዩት ይገኛሉ።

ይህ ዓይነቱ አድራጎታችሁ፡ ምን ማለት እንደኾነ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ወገኖችዎ ኹሉ፡ አኹንም፡ እንዴት ልታውቁትና ልትገነዘቡት እንዳልቻላችሁ ያስደንቃል።

በዚሁ፡ በረዥሙ ዘመናት፡ ይኸው ጸሎት፡ እንዳለ ሲጸለይ መኖሩ፡ እንኳንስ፡ ይህን መሥዋዕትነትና ቤዛነት ለከፈሉት፡ ለእግዚአብሔር እም ቅድስት ድንግል ማርያም እና ለተወዳጅ ልጇ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅርና፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ለኾኑት፡ ነቢያትና ሓዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታትም ቢኾን፡ እጅግ አሳዛኝ እንደሚኾን፡ በማንኛውም አስተዋይ ሰብኣዊ ፍጡር ዘንድ፡ በቀላሉ ሊታወቅ የሚችል፡ ቊም ነገር ነው።

ይኸውም፡ ከዚህ ጸሎት የተነሣ፡ "አምላክ ሰው ኾነ! ሰውም፡ አምላክ ኾነ!" የሚለው መለኮታዊ ምስጢር የተከሠተባት፥ እንዲሁም፡ "ብኪ ድኅነ ዓለም!" ማለትም፡ "ፍጥረተ ዓለሙ፡ በአንቺ ዳነ!" የሚለው፡ ታላቁ እግዚአብሔራዊ እውነታ የተፈጸመባት፥ እግዚአብሔር እም (እናት)፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በእርሷ የኾነውና እርሷ ያደረገችው ኹሉ፡ እንደእርስዎው፡ በዚህ ጸሎት፡ ተጠምደው በኖሩት ዘንድ፡ ከንቱ ኾኖ፥ እንደከንቱም ተቆጥሮ መኖሩ፡ እውን በኾነውና እየተካኼደ ባለው፥ በዚሁ ድርጊታችሁ ይረጋገጣል።

ልጇም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ ከእርሷ፡ በሰውነት ተወልዶ፡-

ለሠላሳ ሦስት ዓመታት፡ ከክፋት ኃይላት የቀረቡለትን፡ የተለያዩ ጽኑ ፈተናዎችንና ከባድ መከራዎችን፡ በፍጹም ፍቅርና ትዕግሥት በማስተናገድ፡ ድል ካደረገ በኋላ፡ የሰውን ባርነትና የዲያብሎስን ገዢነት ሽሮ፡ ፍጹም ዘለዓለማዊ ነጻነትን፥

ደግሞም፡ በመስቀል ላይ፡ ሥጋውን በመቍረስ፥ ደሙንም በማፍሰስ፡ "ሓሰት" ያስከተለውን፡ የኃጢአትን ቀንበር አስወግዶ፡ ፍጹም ዘለዓለማዊ ንጽሕናንና ቅድስናን፥

በመጨረሻም፡ እኒህ ኹሉ ጥፋቶች፡ በዋጋነት ያስከፈሉትን፡ የሞት ጽዋን በመቀበልና ተገንዞ በመቀበር፡ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ፡ ፍጹም ዘለዓለማዊ ምሕረትን፥ ትንሣኤንና ዕርገትን፡ ለእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡሩ ማቀዳጀቱን፡ እንደኦሪታውያኑ አይሁድ፡ መካድ በመኾኑ ነው። አዎን! ያልተቀበሉትን፥ በመጨረሻውም ተቃውመው የገደሉትን አይሁድን በመምሰል፡ ራስን፡ ወደይሁዲነት መመለስ በመኾኑ ነው። አዎን! ገና፡ በኦሪቱ ቀንበር ተቀፍድደው እንደሚኖሩትና "መሢሕ፥ እርሱም ክርስቶስ፡ ገና ይመጣል! አልተወለደም" እያሉ፡ እንደሚጠብቁት አይሁድ፡ ራስን ይሁዲ ማድረግ ነው።

በዚህም ድርጊት፡ ለመላው ሰብኣዊ ፍጡር፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም የተገኘውን፥ ኹለት ሺህ ሰባት ዓመታትን ያስቈጠረውንም፡ ዘለዓለማዊዉን የዘመነ ነጻነትና የዘመነ ምሕረት፥ የዘመነ ትንሣኤም ሕይወት፡ እንደገና፡ ወደ ሦስት ሺሁ፡ የአይሁድ ዘመነ ኦሪት፥ ከዚያም ዐልፎ፡ ወደሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰባቱ፡ ዘመነ ፍዳነትና ዘመነ ኵነኔነት መልሶ መዘፈቅ ይኾናል።

ይህ፡ ከላይ የተገለጸው፡ አሳዛኝና አሳፋሪ ኹኔታ፡ ተቀባይነትን አግኝቶ፡ እየሠራ ያለው፡ በአረማውያኑ አሕዛብ፥ በኦሪታውያኑ አይሁድና በባለቍርዓናውያኑ እስላሞች፥ እንዲሁም፡ ኦርቶዶክሳውያኑን ግብፆችን በሚያካትተው፡ በወንጌላውያኑ ክርስቲያኖች ዘንድ እንጂ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች በኾኑት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ አይደለም።

እኒህ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ "የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያ ልጆች!" የኾኑትማ፡ የእግዚአብሔርን እውነት፥ ይህችውም እውነት፡ ሰው ኾና፡ በእውን ያደረገችውን፡ ዕፁብ ድንቅ፡ ትስብእታዊና መለኮታዊ ትንግርት አውቀውና ተቀብለው፥ ሃይማኖታቸውም አድርገው፡ ይኸው፡ በምግባር እየፈጸሙት መኾናቸውን፡ ከዚህ ጋር አያይዘን በላክንልዎ፡ የ"አቡነ ዘበሰማያት"ን እና የ"አ ማርያም እምነ ዘበሰማያት"ን ጸሎታት፡ የግእዙንና የኢትዮጵያኛውን ዝግጅት፡ በገዛ ዓይንዎ ተመልክተውና አንብበው ይገነዘቡታል።

በዚህ፡ የ"አቡነ ዘበሰማያት!"ን እና የ"አ ማርያም እምነ ዘበሰማያት!"ን ጸሎታት በሚመለከት፡ የበለጠ ለመረዳት ቢፈልጉ፡ ዝርዝር ማብራሪያዎችን በያዘው፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ በተዘጋጀው፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡ ኹለተኛ መጽሐፍ" በሚለው፡ ዕትም፡ በምዕራፍ ፰፡ ከገጽ ፪፻፲፩-፪፻፴፰ ድረስ የሠፈረውን ሰፊ ሓተታ ያንብቡ!

ምናልባት፡ ይህን ማድረግ ካልቻሉ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ "ንሕነ ኢትዮጵያውያን ወኢትዮጵያውያት" በሚል መግቢያ፡ "የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያ ልጆች!" የኾኑት ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ ዘወትር የሚደግሟቸውን፡ **"ጸሎተ ሃይማኖት፡ ዘኢትዮጵያ።"** እና **"ጸሎተ ኪዳነ ቃል፡ ዘኢትዮጵያ።"** ከእነዚህም ጋር አያይዘው፡ **"ጸሎተ ስባሔ ለእግዚአብሔር፡ እለ ያቄርቡ ሎቱ፡ ኢትዮጵያውያን ወኢትዮጵያውያት።"** እና **"ጸሎተ ሱላሜ፡ ለድንግል ማርያም፡ እለ ያቄርቡ ላቲ፡ ኢትዮጵያውያን ወኢትዮጵያውያት።"** የተባሉትን፡ የኢትዮጵያ እና የልጆቿ የሃይማኖት ጸሎቶችን ይመልከቱ!

እነዚህ ጸሎታት፡ በግእዝ ብቻ ሳይኾን፡ በኢትዮጵያኛና በእንግሊዝኛ ጭምር ተዘጋጅተው፡ በጎዋ ሰሌዳችንና በፌስቡክ ገጾቻችን ላይ፥ በዐዋጅ መልእክቶቻችንና በመጻሕፍታችንም ውስጥ ስለሚገኙ፡ እየፈለጓቸው ሊመለከቷቸው ይቻልዎታል።

እንግዴህ፡ በመደምደሚያው፤ ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ፥ ለእርስዎና እርስዎን ለመሰሉትም ኹሉ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** የኾነችው፡ ራሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የምትላችሁ፡ ይህ ነው፡-

«እንደቀድሞዎቹ ኹሉ፡ በአኹኑ ጊዜም፡ እየራሳችሁን፡ ወደርኩስ መንፈስነት ለውጣችሁ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ የእኛ ተቃዋሚና ጠላት፥ የሰይጣናትና የአጋንንት፥ የርኩሳን መናፍስትም አለቃ ከኾነው፡ ከእባቡና ከዘንዶው ዲያብሎስ ጋር፡ ኅብረት ፈጥራችሁ፥ የእርሱም ተገዦችና መሣሪያዎች ኾናችሁ፡ ፍጥረታችንን፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ በምመራውና በማስተዳድረው፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ያመፃችሁ፡ እናንት፡ ክፉዎችና ከሃዲዎች፥ ዓመፀኞችና የአምልኮ አመንዛሪዎች፥ አስመሳዮችና ግብዞች!

«በእውነተኛ ንስሓ፡ ወደእኛ እንድትመለሱ፡ ከሚያስፈልገውና ከሚገባው በላይ፡ በቅዱሱ ኪዳን ታማኞች አገልጋዮቻችን አማካይነት ብቻ ሳይኾን፡ በእኔና በልጄ በወዳጄ ኢየሱስ መሢሕ ሳይቀር፡ ብዙ ተነግሮዋችኋል። አኹንም፡ እየተነገራችሁ ነውና፡ ተመለሱ!

«አንተም ዲያብሎስ! እኛ በፈጠርነው፥ እኔና ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሢሕም በተቤዠነው ፍጥረታችን ላይ፡ አንተ፡ በፍጡርነትህ፥ በክፉነትህም፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ የባለቤትነት መብትና የገዢነት ሥልጣን፥ የአጥቂነትም ኃይል፡ ፈጽሞ የለህም፤ ወደፊትም፡ አይኖርህም። ምንጊዜም፡ ሊኖርህም አይቻልም።

«ይህን ዓይነቱን፡ ምትሓታዊ መብት፥ ሥልጣንና ኃይል የሰጡህ፡ እየራሳቸውን፡ በጭፍራነት፡ ለአንተ ያስገዙት ብጤዎችህ የኾኑት፡ ርኩሳን መናፍስትና ክፉዎች የኾኑት፡ የሰው ወገኖች ናቸው።

«የሺሁ ዓመት የእሥራትህ ዘመን፡ በ፪ሺ (በኹለት ሽህ) ዓመተ ምሕረት ተፈጽሞ፡ ለጥቂት ጊዜ ስለተፈታህ፡ እየራሳቸውን፡ ለአንተ ያስገዙትን፡ ክፉዎች ሰዎችን፡ እርስ በርሳቸው የምታጫርሳቸው ከመኾንህ በቀር፥ ሌሎቹንም፡ መላውን የጥፋት ሠራዊትህን፡ እሳት፡ ከሰማይ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ የምትበላቸው ከመኾኑ በቀር፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ማኅተም፡ በየግንባራቸው በኾነላቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን ልጆቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ላይ፡ ምንም ዓይነት ጉዳትን ልታደርስባቸው እንደማትችል ታውቀዋለህ።

«ከዚህ እውነታም ጋር፡ ጭፍሮችህ ስለኾኑት፡ ስለእነዚሁ፡ ስለርኩሳኑ መናፍስትና እነርሱን ስለመሰሉት፡ ስለክፉቆቹ ሰብአውያን ፍጡሮቻችን ስንል፡ እኔና ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሢሕ፡ በከፈልነው መሥዋዕትነትና በፈጸምነው ቤዛነት፡ በፍጹም ድል ኾነህ፡ ይኸው፡ ሓሳዊውና ምትሓታዊው፡ የክፋት መብትህ፡ እንደተወገደና ግፈኛው ሥልጣንህ፡ እንደተሻረ፥ የጭካኔ ኃይልህም፡ እንደተደመሰሰ አይተሃል።

«ዳሩ ግን፡ በእኛ በኩል፡ ለፍጥረታችን ያቀዳጀነውን፡ ይህን ኹሉ የድልና የቸርነት ጸጋ ባለመቀበል፥ እንዲያውም፡ ይኸው፡ ሓሳዊዉና ምትሓታዊው፡ የክፋት መብትህ፡ እንዳልተወገደና ግፈኛው ሥልጣንህ፡ እንዳልተሻረ፥ የጭካኔ ኃይልህም፡ እንዳልተደመሰሰ በመቍጠር፡ ዛሬም፡ በዚያው፡ በተለመደው ትዕቢትህና ድፍረትህ፡ በፍጥረታችን ላይ "ያለኝ፡ የባለቤትነት መብቱና የገዢነት ሥልጣኑ፥ የአጥቂነት ኃይሉም፡ አኹንም፡ የእኔ ነው!" እያልህ፡ ፍጡሮቻችንን፡ በሓሳዊው ጦርህ እየወጋህ ማታለልህን፡ እንዲህ፡ ከቀጠልህ ግን፡ አንተም፥ ሠራዊትህና ጭፍሮችህም፡ ወዮላችሁ! ብዙ ዋይታ አለባችሁ።

«ስለዚህ፡ ከኾነልህ፡ አንተም፥ ሠራዊትህና ጭፍሮችህም፡ በንስሓ ትመለሱ ዘንድ፡ ይኸው፡ ለመጨረሻ ጊዜ፡ ዛሬም፡ ዕድሉ ቀርቦላችኋል።

«ከዚህ በኋላ፡ አንተ፡ ዲያብሎስ፡ ከነሠራዊትህ፥ እናንተም፡ የእርሱ ጭፍሮች የኾናችሁት፡ ሰብአውያንና ሰብአውያት ፍጡሮቻችን ኹሉ፡ እስካኹን፡ በግትርነት፡ አጽንታችሁ ባቆያችሁት እምቢተኛነታችሁ ከቀጠላችሁ፡ በዓለም ፍጻሜ፡ እንደምትቀበሉት ያወቃችሁትን፡ ዘለዓለማዊ፡ የፍርድ ቅጣት፡ እንደገና ስሙት!

«እርሱም፡ እንዲህ የሚለው ነው:- "ወዐገትዋ፡ ...ጎግ ወማጎግ፡ ...ለትእይንቶሙ ለቅዱሳን፥ ወለሀገር ቅድስት። ወእምዝ፡ ወረደት እሳት እምሰማይ፡ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ወበልዐቶሙ። ወለዝክቱኒ ሰይጣን፡ ዘያስሕቶሙ፡ ወደይዎ ውስተ ዕዘቅተ እሳት፥ ወተይ፡ ኀበ ሀሎ፡ ዝክቱ አርዌ፥ ወሓሳዌ ነቢይ፡ ከመ ይደየኑ፡ መዐልተ፤ ወሌሊተ፡ እስከለዓለመ ዓለም። ...ወተኰነኑ ኵሎሙ ...ምውታን... በከመ ምግባሮሙ። ...ወለኵሉ ዘኢይትረከብ፡ ጽሑፍ፡ ውስተ መጽሓፈ ሕይወት፡ ይወድይዎ፡ ውስተ ገሃነም፡ ዘእሳት።"

«ማለትም፡ "...ጎግና ማጎግ፡...የቅዱሳንን ሠፈርና ቅድስቲቱን አገር [ኢትዮጵያን] ከበቡ። እሳትም፡ ከሰማይ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ፡ በላቻቸው። ያሳታቸውም ዲያብሎስ፡ አውሬውና ሓሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት፡ ወደእሳቱና ወደዲኑ ባሕር ተጣለ። በዚያም፡ ለዘላለም፥ እስከዘላለም፡ ቀንና ሌሊት ይሠቃያሉ። ...ሙታን፡ ኹሉም፡ እያንዳንዳቸው፡ እንደየሥራቸው፡ ፍርዳቸውን ተቀበሉ። በሕይወትም መጽሓፍ ተጽፎ ያልተገኘው፥ ማንኛውም፡ በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።" (ራእ. ፳፥ ፱፤ ፳፥ ፲-፲፭።)

«እስከዚያው ድረስ ግን፡ አዎን! "ወዮላችሁ! ብዙ ዋይታም አለባችሁ!" ያልኋችሁ፡ የልቅሶና የጥርስ ማፋጨት፡ ቀዳሚ መከራና ሥቃይ የሚጠብቃችሁ፥ የሚደርስባችሁም ስለኾነ ነው። (ማቴ. ፳፬፥ ፩-፲፬። ፳፭፥ ፵፩።)

«አዎን! እንግዴህ፡ የእኔዪቱ የኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ "ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕለ ኖኅ፡ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ፡ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው።"

«ማለትም፡ "በኖኅ ዘመን እንደኾነው፡ እንዲሁ፡ የማርያም ልጅ መምጣት ደግሞ ይኾናል።" እንዳለው ኹሉ፡ ዛሬም፡ እናንተን፡ ኹላችሁንም፡ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣንና ኃይል፡ መላዋ፡ ኢትዮጵያ ከኾነችው፡ ከዓለም ምድረ ገጽ፡ ጨርሳ ልታስወጣችሁና ልታስወግዳችሁ፥ ልትደመስሳችሁም ተነሥታለች። (ማቴ. ፳፬፥ ፴፯-፴፱።)

«ይህም የሚኾነው፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዓለም ሰዎች ዘንድ፡ በስሜ፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ ከተከለለችው ምድር ብቻ ሳይኾን፡ በእኔና በተወደደው ልጄ መድኃኒትነትና ቤዛነት፡ ከሓሰቱ ኃጢኣትና ከክፋቱ ፍዳ፥ ከሞቱም ዕዳ፡ ፈጽሞ ነጻ ከወጣው፥ የእኔ፡ የኢትዮጵያ፡ አጠቃላይ ምስፍና ከኾነውም፡ ከመላው ዓለም ጭምር ኹሉ ነው።

«ይህ እውነታ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ በፍጹም ፍቅሩና በረቂቅ ኃይሉ፡ ለዚች፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥቱ፡ በገሃድ እያካኼደውና እያከናወነው ባለው፡ በመጨረሻው ተአምራዊና ትንግርታዊ ሥራው ተከሥቷል። ይኼም፡ የመጨረሻው ተአምራዊ ትንግርት፡ እየተፈጸመ ያለው፡ በአኹኑ ጊዜ፡ እርሱው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ እውነቱን እያሳወቃቸውና በእርሷ እየመራቸው፥ እየጠበቃቸውና እያጸናቸውም፡ ኪዳናዊ አገልግሎታቸውን፡ በፍጹም ቅንነትና ትጋት፥ ታማኝነትና ጽናት፡ በያሉበት በሚያካኺዱት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ "የእግዚአብሔር እና የእኔ፡ የኢትዮጵያ ልጆች" በኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት አማካይነት መኾኑ ነው።

«እነርሱም፡ ይህንኑ ኪዳናዊ አገልግሎታቸውን የሚያበረክቱት፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና የእግዚአብሔር መንግሥት ንግሥት፥ ተዋሕዶዪቱ ሃይማኖትና እናት አገር በኾንሁት፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም ስም፥ እንዲሁም፡ ድል አድራጊው አንበሳና ዘለዓለማዊው ካህን ንጉሥ በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ልጄ ወዳጄ፡ በኢየሱስ መሢሕ ስም ስለኾነ፡ ተፈጻሚነቱና ፍሬያማነቱ እሙን ነው።

«በዚህም፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያዪቷ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ "ወእመሰ አነ፡ በመንፈሰ እግዚአብሔር አወጽኦሙ ለአጋንንት፡ ዮጊ በጽሐት ላዕሌክሙ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር። ወአልቦ ዘይክል መኑሂ፡ በዊአ ቤተ ኃያል፤ ወበርብሮተ ንዋዩ፡ ለእመ ኢቀደመ አሢሮቶ ለኃያል፤ ወእምዝ፡ ቤቶ ይበረብር። ዘኢኮነ ምስሌየ፡ እድውየ ውእቱ፤ ወዘኢይትጋባእ ምስሌየ፡ ይዘርወኒ ዝርወተ።"

«ማለትም፡ "እኔ ግን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ፡ አጋንንትን የማወጣ ከኾንሁ፡ እንግዴህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፤ ወደእናንተ ደርሳለች። ወይስ፡ ሰው፡ አስቀድሞ፡ ኃይለኛውን ሳያሥር፡ ወደኃይለኛው ቤት ገብቶ፡ ሀብቱን ሊበረብር፡ እንዴት ይችላል? ከዚያ ወዲያ፡ ቤቱን ይበዘብዛል። ከእኔ ጋር ያልኾነ፡ ይቃወመኛል፤ ከእኔ ጋር የማያከማችም፡ ይበትናል።" ያለው ቃሉ ይፈጸማል።» (ማቴ. ፲፪፥ ፳፰-፴።)

\+ + +